ሰንደቅ ዓላማችን

መጋቢት 20/2ሺ ህ 1

ለአሜሪካ ድምጽ የአማርኛው ክፍል አዘጋጆች

ሰንደቅ ዓላማችንን በተመለከተ ከኤንጅኒር ኃይሉና ከኹለት የገዢዎቹ ባለሥልጣኖች ጋር ያኪያሄዳችሁትን ቃለ-ምልልስ ያስታዉሷል፤፤
አስቀድሜ ግን ስለመልካምና አርኪ እንዲሁም አዝናኝ ዝግጅቶቻችሁና ቅንብሮቻችሁ፦ መልካም ፌዞቻችሁንና ቀልዶቻችሁን ሳልረሳ፦ ላመሰግናችሁ፤፡ ከአቃቂ እንዳታልፍ እናደርጋታለን የተባለችውን አገራዊ ቋንቋችንን የተማሩና ዐወቅን የሚሉ ከሌሎች ቋንቋዎች ሊደቅሉ ሲፈል 'ቀለብ!' አርጋችሁ (ማረማችሁን/ማስተካከላችሁን ሳታስታውቁ) ለምታደርጉት ውለታም ቡራኬዬ ይድረሳችሁ።
በኢትዮጵያችን ላይ አቅኚዎች ነን የሚሉት በተለያየ መልክ ሲዘመቱ ክፍለ-ዘመናት ተቆጥረዋል። ጀግኖች ልጆችዋ ተንኮላቸውን በጥበብና በዘዴ፦ ኃይል ሲፈልጉም በጀግንነት መክተው አገራቸውን አሳፍረው አቆይተው ነበር፤፡ ጠላቶቻችን ሌሎች የጥቁሮችንና የብጫዎችን አገሮች አንበርክከው ሕዝቦቹን በባርነት ሊገዙ ሃብታቸዉን ሊቦጠቡጡ የቻሉባቸው ዘዴዎች፦ እንደ ባላባቶቻቸውን በብልጭልጭ ቆሳቁሶች እያታለሉ፤- ጠጠር ሲሉባቸውም በሃይማኖትና በጎሳ እንዲሁም በቋንቋ እየከፋፈሉ እንደነበር ዕድሜ የሰጣቸውና ፊደል የቆጠሩት ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ኹሉ ያውቁታል። በእዚህ ዕድሜ ክልል ዉስጥ ያለነው እያነስን፦ የሚበዙት የዚህ ዕድል ያልደረሳቸው፡ በአባት እናት የመመከርና ከእናት አባት ለመማርም እንደዚሁ ያልቻሉ ብዙሃን ናቸው። ይኸም፦ የቀደሙት እያለፉ ወጣቶች እየተተኩ መሄዳቸው ፤ የነበረና ያለ የሚኖርም ስለኾነ ከተቻለ የቀደሙት ለተከታዮቻቸው ተመክሯቸዉን ማስተላለፍ ይገባል።
ስለዚሁም የአዛውንትነት ግዴታዬን ለመወጣት ልሞክር። ሳናውቃቸው፦ ሳንደርስባቸው፦በልጅነታችን የመልካ ምድርን ( ጂኦግራፊ) የምንማርባቸው መጽሓፍት እንደእኛ አገር የሚቋምጧቸዉን አገሮች " ለነጮች ሠፈራ የሚመቹ/የሚስማሙ " ይሏቸው ነበር። አባቶቻችን አገራችን ለኛ ትስማማለች/ትመቻለች ብለው ጠላትን በብቃት መከቱ፦ ጠላቶችም፦እንዴት! ብለው ቢመጡ ጎጻን ኹሉ እንድሚያውቀው አድዋ ላይ በማይረሳ መስተንግዶ ሸኟቸው።
የኹለተኛውንም የኢጣልያን ድፍረት ጌታ በጥበቡ አከሸፈው።
በምርምር የመጠቁትና የደረጁት ይኸንንም መረመሩት አልጠግብ ባዮች፦ ባጭሩ ኢትዮጵያችን በአንድ ን.ነ. የምትመራ፦ አንድ ሰንደቅ ዓላማ፦ አንድ አገራዊ ቋንቋ ያላት፦ ልዩ ልዩ ሃይማኖቶችም ቢኖሯት ተከባብረው፦ ተከታዮቻቸውም ተዋድደውና በማንኛዉም የኑሮ ሂደት ውስጥ ተጋግዘው ጠላት ሲመጣም በአንድ የሚመክቱ፦ (የመንግሥቱ ሃይማኖት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሲኾን እርሱም ለትምሕርት ለታሪክ ምዝገባ እና አንድነትን ለማጠንከርያ የሚጫወተው ሚና ጠንካራ እንደኾነ ዐውቀው) በቀጥታ መምጣቱ የማያዋጣቸው መኾኑን ሲደመድሙ፦ኢትዮጵያን ለመግዛት ዘውድን ማጥፋት የተቀዳሚ ተግባራቸው መኾኑን አምነዉበት፤፤ ይኸን ግዳጃቸዉን ያለብዙ ልፋት በስድሳውቹ ውስጥ የነበሩት የሠራተኛና የመምሕራን ማሕበራት፦ ተማሪዎች

እንዲሁም ዐወቅን ባዮች ምሑራን ዘውድን አንገዳገዱት። በተመሳሳይ ዐወቅን ባዮች ወጣት መለዮ ለባሾች የዘውድን ሥርዐት ገረሠሱት። " አህያ ጭዱን እንጂ ገደሉን ሳያይ ..." እንደሚባለው አገራቸውን ሳያውቁ የውስጥና የውጭ ጠላቶቿንም ሳያስቡ አገር - ወገንን ለዚህ ውርደትና፣ ችግር ችጋር ስደትና መበታተን ዳረጉ፤፤ የዘመነ መሳፍንትን ታሪክ ቢያዩ ወይም ስለሱ ቢጠይቁ መሳፍንት ወደ 70 ዘመናት ሲገዙ በንጉሠ ነግሥት ስም ነበር! አገር ወገናቸውን ያውቁ ነበርና ! አገርና ወገን ያልተቀበለው መንግሥት ዕድሜ ሊኖረው እንደማይችል መንግሥታት ሲለዋወጡም አገርን ለጠላት መዳረግ እንደሚያስከትል በመገንዘብ ጥንታውያን አበው ስምን አልፈለጉም፤፤
አብዮት ደንቆሮዎች እጅ አትውደቅ የሚባለው ለዚህ ይኾን?

ወደ ሰንደቅ ዓላማው ልመለስ፤፡ ሰንደቅ ዓላማችን ለኢትዮጵያውያን ብቻ የአንድነትና የነጻነት ምልክት ሳይኾን ለመላ አፍሪካም ኾነ፤፤ ክቡር ኤንጅኒር ኃይሉ እንደጠቀሰው አንድ አምስት አገሮች የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ ሦስቱን ቀለማት አንዳንድ ምልክት ( ኮከብ) እያደረጉ:- ቅርጾችንም እየለዋወጡ የራሳቸው አደረጓቸው።
ሌሎቹም ሦስቱን ቀለማት ይዘው ሊላ በመጨምር ኢትዮጵያችን ለነጻነታቸው በተለያዩ መንገዶች የረዳቻቸውና ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት መቋቋምም መሪ ተዋናይነቷን በመዘከር ባለውለተኛነታቸውን ለማረጋገጥና ለወደፊቱም አንድነታቸውን ዕውን ሲያደርጉ በሰንደቅ ዓላማ ቀለማት በኩል ችግር እንዳይደርስ ለመዘጋጀት እንደነበር ከአንዳንድ መሪዎች ተረድቻለሁ፤፡ የዚምባብዌን ሰንደቅ አላማ ቀለማት መመልከቱ ለአብነት ይረዳል።

ይኸን ኹሉ በንቃት የሚጠባበቁ የውጭ ጠላቶቻችን፦ የዓለም ንጥረ ነገር እያለቀ ሕዝቡ ግን እየበዛ በሚሄድንት ወቅት የቻሉና፡ የተራቀቁት ወደ ጠፈር ሲመጥቁና ጠፈር ላይ መኖር መቻል አለመቻላቸውን ቢያጠኑም አፍሪካን መቋመጣቸው አልቀረም።አፍሪካ በቅርቡ ልጆችዋ ወደ ቢሊዮን የሚደርሱ ስለኾነ " ቀንደኛዋን ኢትዮጵያን ካልከፋፈልናትና ቁጥጥራችን ውስጥ ካላስገባናት አፍሪካን ማጣታችን ነው" ብለው ከፋፋዮችንና የታሪክ ደብዝ አጥፊዎችን ከዉስጥ ጫኑብን። እኛም በተላላነት፡ " እስከ መጨረሻው እየገዛናችሁ በመቦጥቦጥ አገራችንን እንገነባለን። መግዛት እማንችልበት ደረጃ ከደረስን ገንጥለንና ተገንጥለን ወደ መጣንበት እንመለሳለን።" እያሉ ሳይደብቁ በድፍረት እየነገሩን አንሰማ ብለን እንቦጠቦጣለን- እንታሰራለን- እንገደላለን፤፡ ልይበልጥ ደግሞ እንዋረዳለን። እስከ መቼ? ጃል?
ጀግኖቹማ እንደ ክቡር ራስ አበበ አረጋይ ዓይነቶቹ ከአዲስ አበባ በሃምሳ ኪሎሜትር ርቀት ላይ ኾነው ጣሊይንን ያንገበገቡት ፀሎት ላይ እያሉ ጠላት መጣ ደረሰ - በጣም ብዙ ነው እያለ ቃፊር ሲወተውት ፤- ፀሎታቸውን ሲጨርሱ " ታዲያ ሞተን አንጠብቀው ።" ያሉት እኛ ግን የዘንድሮ ልጆች - ሰዎች በቁም እየሞትን ነው ሞትን የምንጠብቀው።
ስለዚህ ነው ገገሮዎቹ ሲገቡ በቀደምት በሰንደቅ ዓላማችን ላይ የዘመቱት። ያስገቧቸው ፍላጎትና ዕቅድ ነውና! በሸንጓቸው ላይ " ሰንደቅ ዓላማችንን እንኳን ሰዉ ግመሎቻችንም ያውቃሉ፡" ብለው ያሳፈሩልንን፦ ስለዚህም ዕውነተኛውን የኢትዮጵያ ልጅ የአፋሩን ባላብት ክ. ቢትወደድ አሊ ሚራህን በአክብሮትና በወገናዊነት እንወድዳቸዋለን እናከብራቸዋለን።
የኢትዮጵያ ሕዝብም ሴቷ ሻሽ ቀሚስ መታጠቂያና አምባር አርጋ ስትዋብበት ወንዱም ከግምባር ላይ ገርዳሳ ጀምሮ በምን አላጌጠበትም? " የሚሰማ ጆሮ

*ያለው..የሚያይም ዓይን ያለው…” ገዢ ቢኖር ይኸ ባልኾነም ነበር። ተልዕኮው ከውጪ የኾነ “ ጌታዋን የተማመነች በግ ላቷን ከውጪ ታሳድራለች “ እንደሚባለው ሕዝብን ከመጤፍ በመቁጥር ‘ ዓይኤን ግምባር ያርገው ጆሮዬም ዳባ ይልበስ” ጠብመንጃ እስከያዝሁ፦ ሆዳሙንም በገዛ ገንዘቡ እስከገዛሁት ብለው ገዢዎች ግፍና ንቀታቸውን ገደብ አሳጡት፤፤ ያነጋገራችኋቸው ባለሥልጣኖች አንድ ፌዘኛ ከኹለት መቶ ዓመት በፊት የተናገረውን ትምሕርታዊ ጥቅስ አስታወሱኝ።*

*“ የብዙ ሰዎች ችግር “ ይላል ፌዘኛው አስተማሪ “ይኸን ያህል ድንቁርናቸው አይደለም፦ ያልኾኑትን ነገሮች ማወቃቸው እንጂ ! “*

*የባለሥልጣኖቹን አነጋገርና ድምፀቱን በትክክል መግልጫ ቃላትን አገራዊ ቋንቋችን ሳያሳጣን መልካም ሥነምግባርንና ባህልን በማክበር፤ “ዘበናይነት የተሞላበት ነበር፦” ማለቱ ይብቃ!*

*ባንድ በኩል እንዴት ይፈረድባቸው? ያሉትን ባለሥልጣኖች በቴሌ ስናያቸው በመጀመርያው ገጽ ኹለተኛው ረድፍ ላይ እንደተገልጸው ዕድሜ ውስጥ ያሉ ናቸው።*

*ስሜታዊ ተረታቸውን አልፈን በባለ ዘውዶች አርማና በአገራችን ሰንደቅ አላማ መኻል ያለዉን ልዩነት ቢያውቁ ባልተሳሳቱም ነበር፤ ማለቱ ከጭካኒ ያድናል ፤*

*አረንጓዴ ብጫ ቀይ የኢትዮጵያችን ሰንደቅ አላማ ቀለማት ናቸው እያንዳንዱም ቀለም ባለ ትርጉም ነው። የአንዱን ኢንጅ. ኃይሉ አስታውሶናል። መኻሉ ላይ ሰንደቅ አላማችንን የያዘ አንበሳም የኖረበት ጊዜ እንደነበር ስምቻለሁ፤፡ የነበርንበት የ ቀቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አርማ ግን መኻል ላይ ዘውድ የደፋ ባለወርቅ መርገፍ ሰንደቅ አላማችንን የያዘ አንበ ነበር፤፡ እዚሁም ውስጥ ቅ. ጊዮርጊስ ደራጎኑን ሲገድል ነበረበት። ይኸም የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥነታቸውን የሚያመለክት ነበር።እኔ እንደማውቀው አንበሳንም ከን. ነገሥቱ ጋር ብቻ ማያያዝ “ የይሁዳ አንበሳ” የሚለዉን በመያዝ ይመስለኛል። ይኸም ያለማወቅ ሳይኾን ቀረ ብላችሁ?*

*ስልዚህ ሰንደቅ ዓላማችንን ከአገዛዝ ሥረዐት ጋር ማያያዝ የሚያሳየው እላይ እንደተጠቀሰው “… ድንቁርናቸዉን ሳይኾን ያልኾነ ነገር ማወቃቸዉን ነው” ወይም የገደል ማሚቶነትን ነው። ሳታስተውሉ እንደማትቀሩ ገዢቸው አንድ ጊዜ “ ፌፈራል ሆስፒታል “ አለ አሁን ከአንድ ክፍለ-አገር በስተቀር ኹሉም ይኸንኑ ሲያነበንቡ ይሰማል። ሌሎችም በእርሱ የተነገሩና እንደጥንት ዳዊት ደጋሚዎች ኹኦኡም ደጋፌ-ዐውቂ የሚኾኑባቸው ብዙዎች አሉ። ትኩሱ ግን ጠቅላይ ሚንስትራቸው “ የትምሕርት ፓኬጅ “ በቅርቡ ካለ በኋላ ባገሪቱ ኹሉ “ፓኬጅ ፓኬጅ…” ሲባል ነው፡ ጆሮ እስከሚያደነቁር የሚያዘበዝቡት ከመለስ ታዝዘው ይኾን ከአቃላጭቹ አላውቅም።ወይስ ለመምሰል?*

*“ካላሸንፍካቸው ተቀላቀላቸው፦” የሚል የእንግሊዝኛ ዘይቤ አለ አይደል? ባነጋገራችኋቸው ባለሥልጥኖች “ ለአንዳንድ በዓል እንኳን መያዝ ይቻላል።” ተባልን። ሰንደቅ ዓላማችንን። ወይ ድፍረት?ይኸ ምን አስታወሰኝ መሰላችሁ? ኤርትራ ክ.አገራችን ለ68 እጅግ ረጅም ዘመናት በኢጣልያን ሥር በነበረችበት ወቅት ሕዝቧ ለየዐውደ ዓመታትና ለሠርግና ለቀብሩ በእናት አገሩ አርንጓዴ ብጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማው ክብሩንና ታሪኩን አስከብሮና ጠብቆ ነበር። ደብረ ቢዘን ግን ከነፋሲት እስከ ምጽዋ ይዘቱ ኹለዬም የኢትዮጵያ ስለነበር ክረምት*

ከበጋ በሰንደቅ አላማው እንደተከበረ ሰንደቅ አላማውንም እንዳስከበረ ነበር የጊዜ ነገር “ ነበር ! እንዲህ ቅርብ ኾነ” ክፍለ-አገራአችንን “ ቅኝ አገር” ብለው ሲገነጥሉ በቅኝ አገርነት የማትታወቀውን ደብረ ቢዘንንና ይዞታዋን እንኳን የእኛ ናት ብለው ሊከራከሩ የቤትክርስቲያናችን ገዢ $40 ሺህ ብር “የእንኳን ደስ ያላችሁ” ሰጡ። የማንን ብር? ፌደሪሽን ተብሎ አንድ ሰማያዊ ነገር እንዲያውለበልቡ ሲደረግ ክብሩን ሳያስነካ የኖረው ወገናችን ኹሉ ከእናት አገሩ መቀላቀሉ ፍትፍት ሲኾንለት ሰንደቅ ዓላማውን ማጣቱ ምርቅ ኾነበት።

ስለዚህ፦ አገራችንን አስከብረው ላለፉት አባት እናቶቻችን የሚገባቸውን ክብርና ሞገስ ላለመንሳትና “ ውለታ በጥፊ ትውልድ” ኾነን የታሪክ መዘባበቻ አተላ እንዳንኾን በኢትዮጵያውያንነታችን የምንኮራ ኹሉ ጣልያኖች ለመከልከል ያልደፈሩትንና ሕዝቡን እንዳከበሩት ያኹኑ ትውልድም ታሪኩንና ራሱን ለማስከበር ልጅ ሲወለድ ፤- ክርስቲያኑ ክርስትና ሲያስነሳ ጀምሮ እስላሙም በሃይማኖቱ የሚያከብራቸውን በዓላት ኹሉ ቤቱና ዳሱ/ሆቴሉ ላይ ኹሉ አኩሪ ሰንደቅ ዓላማውን በማውለብለብ ማንነቱን ቢያስከብር ትውልድ ያከብረዋል። ታሪክም አይወቅሰዉም። የቅርቡ በዐል ትንሳኢ ስለኾነ እስላም ክርስትያኑ በ ጥንታዊቱ ብዙ መስዋዕት በተከፈለባት ባንዲራው አገር-ምድሩን ያሸብርቅበት። “ ሃይማኖት የግል አገር የጋራ ነው” የተባለውን ኢትዮጵያውያን ኹሉ ዕውን እንርገው። ክብራችንን ጠብቀን እንከበር! የእስላሞች ወገኖቻችን በዐላት ሲመጡ ኹላችንም በሰንደቅ ዓላማችን አገእራችንን እናድምቅ

ከኹለት ሦስት ዓመታት በፊት የአድዋ በዓል በታላቅ ክብር ሲዘከር ከቦታው የተገኙት ውድ የኢትዮጵያ ልጆች የታሪክ አክባሪዎቹ የትግራይ ተወላጆች የሠልፍ ቦታውን ሲያጥለቀልቁና ሲተምሙ ኹሉም በአገር ልብሳቸው አሸብርቀው በጥንታዊቷ ሰንደቅ ዓላማቸው ደምቀው ሲታዩ እጅግ አኩሪዎች ነበሩ፤፤ የተለጠፈባቸው ተይዘው የነበሩት በመለዮ ለባሾች ብቻ ነበር።
የመለዮ ለባሾችን ካነሳን ለአንድ ወታደር የመጨረሻ የውርደት ሞቱ ሰንደቅ ዓላማውን ሲያስማርክ ነበር። ታዲያ የአባቶቹን ክብር ሲረግጥና ሲስረግጥ ምን ይሰማዋል?! የብሔር- ብሔረሰብ መብትና ዕኩልነት የሚከበር ዓልም-ዐቀፍ ግዲታንና ሕገ መንግሥት ተብዬዉን ተግባራዊ በማድረግ እንጂ ታሪክን በማዋረድና ሕዝቡንም በመናቅ አይደለም። ሲኾን ክብሩን መንግስት ተብዬው ሲረግጥበት ተዉ! ማለት የሰው ልጅ ግዲታ ኔው።

መኢአድ. በአገሩ ሰንደቅ ዓላማ ለመከበርና ለማስከበር ትንሽ ዘዴ ያስፈሊገው ይኾናል።

አቃላጮች ኹሉ ሕገ መንግሥት - ሕገ መንግሥት የሚሉት የኢትዮጵያ ሕዝብ መቼ የተጠየቀበትና ይኹንታዉን የሰጠበት ነው? ምርጫ 97ን ተከትሎ የኃያላን መንግሥታት ተጠሪዎች ኹሉ ተቆርቋሪዎች መስለው ሸንጋዮች ነን ብለው “በሕገመንግሥቱናበሕግ መሠረት” እያሉ እያነበነቡ ቅንጅትን እንዳሸመደመዱት የሚረሳ አለ?
ሕግ-መንግሥት ተብዬውስ የሚከበረው በገዢዎቹ በተነቀሰ ምርጫ ብቻ ነው? በዚህ እንኳን ሕዝብ ምርጫ ይኑረው እንጂ!

ሕገመንግሥት ተብዬዉን ለማጽደቅ በተደረገው ግብዣ ላይ በዚህ ሰነድ ኢትዮጵያን እኛችን አስገባናት” ማለታቸውን ግን የሰማ ብዙ አይመስለኝም። ስፊና ጥልቅ በመኾኑ ለአኹን ልለፈው።

ለማንኛውም ጃንሆይ በ 1934 ለታሪክና ምሳሌ 3ኛአ መጽሓፍ በጻፉት መግቢያ ልዝጋ!

“ ተማሪ ቤት የሠራንላችሁ - አስተማሪ የቀጠርንላችሁ -
ዕውቀትን እንድትገበዩ የምንደክምላችሁ -
አብባችሁ በመማር አፍርታችሁ - አገራችን ተጠቅማ እንድትኮራባችሁ
መኾኑን ዐውቃችሁታል?
አገራችን በትጋት ተምራችሁ እንድትረድዋት
ትፈልጋችኋለችና እንዳትጠፉባት!”

ምንኛ አርቆ አስተዋይነት ነበር። እንደፈሩት በአካልም በግብርም በመንፈስም ጠፉንባት ይኾን!

ከሰላምታ ጋር

ኮማንደር አሰፋ ሰይፉ

የኪስ ስልኪ ቁ 4479 8685 0274

ት